# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ

Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band


*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*የካቲት 1 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

## *የኛው የካቲትና የእነርሱ ለካቲት*

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፤ በአንዲት ሀገር፤ ሁለት የካቲቶች፤ ሁለት ትርጉሞች ተሰጥቷቸዋል። ሁለት ትርጉም በሰጧቸው ወገኖችም በተጻራሪ መዘክር ታስበው ይውላሉ። ዋናው የካቲት፤ በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከበረው ፤ የ 1966ቱ ዓ ም ወርሃ የካቲት ሲሆን፤ በትግራዩ ወያኔ ተገንጣይ ክፍሎች ደግሞ፤ ለካቲት ብለው የሚያወድሱትን ወር ነው።

የካቲት ወር በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአዲስ ታሪካቸው ሂደት፤ አዲስ ምዕራፍ የከፈተላቸው ወር ሲሆን፤ የወያኔዎቹ ለካቲት ደግሞ ኢትዮጵያን ለመከፋፈል አዲስ የአጋንንት በረት የከፈቱበት ወር በመሆኑ በየዓመቱ እነርሱ የግል በዓላቸው አድርገው ይደስቱበታል ። ይደነክሩበታል።

በአሁኑ ወቅት፤ ወርሀ የካቲት፤ ልክ እንደ ወያኔ፤ ክልሎቹ ሁሉ በሁለት ተከፍሏል። አንደኛው የካቲት፤ እንደ ብሄራዊ በዓል ተከብሮና ታስቦ ሲውል፤ ሌላኛው የካቲት/ ለካቲት ደግሞ፤ ጎጠኛው የካቲት ተብሎ እንደ መርገም ጨርቅ ተወግዞ ቀርቷል።

በአጭሩ፤ በአንድ ሀገር የሚኖሩ የአንዲት ሀገር ዜጎች፤ አንዱን ወር ሁለት አድርገው የካቲት/ ለካቲት ብለው የየራሳቸውን ስያሜ እንዲኖረው አድርገውታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የካቲት፤ የኢትዮጵያን አንድነት እንደገና ያስረገጠበት ሲሆን፤ የወያኔው ለካቲት ደግሞ፤ ወያኔ የኢትዮጵያን የመከፋፈል አደጋ በማምጣት፤ ቡታ የሰደደበት ወር ነበር። የቡታ ሰዳጁን ማንነትም በሚከተለው ስንኝ ተቋጥሯል።

" አወይ ቡታ ሰዳጅ፤ አንተ አያ ጨርሴ ፤

ሃሳዊ መስሂ ፤ የአጋንት መነኩሴ

መርዶውን ተናገርከ ፤ የአገር መበታተን፤ ዕኩይን ቅላፄ

ናቡ ከደነፆር፤ የሙሶሊኒ አሽገር ፤ የጎጠኞቹ አፄ ! "

ትብሎ ፤ በሙሾ ምፀት፤ ተቋጭቷል ።

የካቲትን ወር እኛ ስናከብር፤ የተለየ ታሪካዊ፤ ሀገራዊና አብዮታዊ መዘከርን እንዲሁም ሀገር ወዳድነትን አንግበን ነው። የጥንቱ የሀገራችን አኩሪ ታሪክ፤ በየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት፤ የተሃድሶ ምዕራፍ ከፍቶ፤ ለአዲስ ሥርዓት ብሩኅ ተስፋ አንፀባርቆ እንደነበር እናውቃለን። የኢትዮጵያም ሕዝብ፤ ይህንን ብሩህ ተስፋ ፤ በዘርና ሃይማኖት፤ በቋንቋና በክልል ሳይከፋፈል፤ በአንድ ላይ ሆ ! ብሎ በመነሳት፤ በኅብረት

የተቀበለበት ታሪካዊ ወር ነበር ። ከአራጀ- የአፈጀ፤ ኋላ- ቀር ሥርዓት የተላቀቀበት ወር ነበር የ 1966ቱ የካቲት !

በኢትዮጵያው 66 የካቲት፤ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ከዳር እስከ ዳር አንድነታቸውን እንደገና አስረግጠው የየካቲትን ዐብዮት ተቀበሉት። በአንድነት እኩልነት፤ በእኩልነት ነፃነት፤ በነፃነት ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር፤ በዴሞክራሲ አስተዳደር ደግሞ፤ የሀገር እድገትና የሕዝብ ብልፅግና የሚገነባበት ዐብዮታዊ ዓላማ ነበረው፤ የ 1966ቱ የካቲት !

ይህ የካቲት፤ ከወያኔ ለካቲት በምንም መልክና ቅርፅ አይገናኝም። አንዱ ሌላውን ተጻርሮ የቆመ በመሆኑ፤ ወያኔ በሥላጣን ላይ እስካለ ደረስም፤ እሳትና ጭድ እንደሆኑ ይቆያሉ። እሳት፤ በውሃ መጥለቅለቅ እንዳሚጠፋ ሁሉ፤ ዘረኛው ሥርዓትም፤ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አመፅ እሳት-ጎሞራ፤ ከምድረ-ኢትዮጵያ መወገዱ አይቀርም ። የካቲት ዐብዮትም በሀገራዊ ደረጃ፤ በታላቅ ግርማ ሞገስ የሚከበርበት ቀን ሩቅ አይሆንም! ይህ ስኬታማ እስከሚሆን ግን ተዳፍኖ ቢቆይ አያስገርምም ! እሳት ቢዳፈን ግን፤ የሚጠፋ አይደለም !

በዘመናት፤ የተለያዩ ሀገራት የየራሳቸው ዐብዮቶችን አካሄደዋል ። የተካሂዱት ዐብዮቶች፤ የየሀገራቸውን ሕዝባዊ አመጽ የሚያስተጋቡ ነበሩ። እነኝህ አመፃዊ አስተገብኦች እንደ የሀገሮቹ ነባራዊ ሁኔታዎችና እንደ ሕዝቦቹ ጭቆና ብሶት የተለያዩ ሊሆኑ ቢችሉም፤ በመሠርቱ፤ የዐብዮት መፈንዳት በሚሆኑ ምክንያቶች ግን ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት አላቸው ማለት ይቻላል። ለዐብዮት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ሁኔታዎች እንዳሉ ቢታውቅም፤ ለአብነት ያህል ሦስት ነጥቦች ጠቅሶ ማለፉ ይበቃል። እነርሱም :-

1ኛ/ ጨቋኙ ሥርዓት፤ እንደለመደው ሕዝቡን መግዛት እየተሳነው ሲሄድና አቅሙ እየተፍረከረከ ሲመጣ። መንግሥታዊ መዋቅሮቹ የመረጃ አውታሮቹና ሥርዓቱን አቅፈው - ደግፈው ያየዙት አውታሮች ፤ ምስጥ እንደበላው እንጨት ሲፈረካከሱ። የሚያየው ሰማይ ሲደፋበት። የቆመበት መሬት ሲከደው ። ያመነው ፈረስ ሁሉ በደንደሱ ሲጥለው።

2ኛ/ ሕዝቡ፤ የመሪር አገዛዝ ቀንበሩ ከሚሸከመው በላይ ሲሆንበትና አለመገዛትን በአሻፈረኝነት ሲገልፅ። በገዥና በተገዥ መካከል ያለው ቅራኔ ሲፋፋም። ለአመፅ የተነሳሳው ወገን፤ ሰኔና ሰኞ ሲገጣጠሙለት ። ታጋዩ ሕዝብ፤ የልብ -ልብ ሲሰማው። የኃይል ሚዛኑ ወደ አመጹ ሲያጋድል ።

3ኛ/ እና ደግሞ ሌሎች ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች ( ዖብጀክቲቭ- ሳብጀክቲቭ ኮንዲሽንስ) ተሟልተው ሲገኙ ነው ።

እነኝህ ሦስት መሠረታዊ ሁኔታዎች ተሟልተው ቢገኙም እንኳ፤ ሁኔታዎቹን የሚከታተልና ሕዝቡን የሚመራ መሪ ድርጅት መኖሩ ደግሞ ወሳኝ ነው። ይህ ባለመኖሩ፤ የኢትዮጵያ ዐብዮት እንዲህ ሆኖ ቀረ። የማንም መጫዎቻ ሆኖ ቀረ። ባለቤት የሌለው ዐብዮትና መሪ የሌለው ጦር አውላላ ሜዳ እንደሚቀር የታወቀ ነው ። ደርግ የየካቲትን ዐብዮት ከሕዝብ ነጥቆ ብዙ ጥፋት ካዳረሰ በኋላ፤ ዐብዮቱን በክሎ

ሀገሪቱንም ለገንጣይ- አስገንጣይ አስረክቦ ሄደ። እርሱም ሀገር አጥፍቶ ጠፋ። አጥፊና ጠፊ ሲጠፋፋ፤ ሀገር የሚያድን ሰውም ጠፋ ! ዛሬ፤ የኢትዮጵያ፤ ሕዝብ መሪ በመብራት እየፈለገ ይማስናል ! ይባክናል !

" እንከራተታለሁ በባዕዳን ጓሮ፤ በፈረንጅ በረንዳ፤

ቤቱ ተቃጥሎበት፤ ልጆቹ አልቀውበት፤ ትዳሩ ፈርሶበት፤ ከብቱ እንደተነዳ ። "

እየተባለ ሙሾ ቢደረደር፤ ከዕለት መፅናናት ያለፍ ፋይዳ አያመጣም ። ማንም አይዞህ የሚል የለም፤ ዛሬ ! ሁሉንም አይተነዋል ! ታዝበነዋልም!

በበርካታ ሀገራት የተካሄዱ ሕዝባዊ አመፆች በወቅቱ የነበሩ ጨቋን አገዛዞችን ከጫንቃቸው ላይ ለማውረድ ቢችሉም እንኳ፤ ለመልካም አስተዳደር፡ ለሕግ የበላይነት፡ እኩልነትን ለማስፈንና ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር አልቻሉም። ሁሉም ዜጋ ያለምን አድልዖ እንደ አቅሙና ችሎታው ሰርቶ፤ የሀገሪቱን ሀብት ተቋዳሽ አልሆነም ። በግለሰብ ደርጃም ሆነ በጋራ የወደፊ ዕድልን በመወሰን ደረጃ ሙሉ ተሳትፎን አላረጋገጠም፡፡ አምስቱን መሠረታዊ መርሆች የሚያሟላ ነፃነትን የተላበሰና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ሲሰፍን አላየም።

የኢትዮጵያ ሕዝብም ቢሆን፤ የዐፄውንና የደርግ አገዛዞችን ከጫንቃው አሽቀንጥሮ ለመጣል ቢችልም፤ ከእነርሱ የከፋ፤ ሕዝብን በጎሳ የሚከፋፍልና ጥላቻን የሚያስፋፋ የወያኔ ዘረኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ተተክቷል ። ይህ ሥርዓት፤ በኢትዮጵያ ከሰፈነ፤ ሃያ አራት ዓመታትን አስቆጥሯል።

በማነኛውም ሀገር የተካሄደው ዐብዮት ፤ ሁሉ የየራሱን መጥፎ የታሪክ አሻራ ጥሎ አልሄደም ማለት አይቻልም ። በዓለም ታሪክ ሂደት፤ በዕስመ- ሥልጣኔ፤ ሃይማኖት፤ ሀገር ማቅናት፤ ሶሻሊዝም፤ የነፃነት ጦርነት ፤ የብሄር ትግል፤ ወዘተ.. ብዙ ግፍና ወንጀል እንደተፈፀመ ሁሉ፤ በዕስመ- አብዮትም እንዲሁ፤ ይህ ነው የማይባል ግፍና በደል መፈፀሙን ታሪክ መዝግቦታል ።

በተለይማ፤ በእኛ፤ ሀገር፤ በአብዮት ስም የተፈፀመውን ይህ ነው የማይባል አረመኒያዊ ወንጀል፤ ሲያስታዉሱት እጅግ ይዘገንናል ! ያንገፈግፋልም። ከዚህ ይበልጥ፤ በእጅጉ እንደ እግር እሳት የሚያንገበግበው ግን፤ ያ ሁሉ የሕዝብ መሥዋዕት ተከፍሎ፤ ጉልቁ- መሳፍርት የሀገር ሀብት- ንብረት ወድሞ፤ ዛሬ ሀገራችን የባዕዳን መጫውቻ ሆና መቅረቷ ነው። እዚህ ላይ አንድ ጉዳይ ልብ ይሏል ! የተጠያቂነት ሚዛኑ ይለያይ እንደሁ እንጅ፤ ኢትዮጵያ አሁን ለገጠማት ሁኔታ ሁሉም በየደረጃውና በየአግባቡ ከተጠያቂነት ነፃ ሊሆን የማይችል መሆኑ ነው ።

" ተከታዩ ወሬኛ ፤ ዳኛው ውሸት ሰሚ ፤

እኛስ ሄድንላችሁ ይብላኝ ለከራሚ "

ቢሉት፤ የጎሊና ዕረፍት አያስገኝም ! በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊከበር የሚገባውን አንድ የካቲት ከሁለት ከፍሎ ፤ የገመድ ጉተታ ፖለቲካ ጨዋታ ቢያደርጉ፤ የሀገሪቱን ስር የሰደደ ችግር አይቀረፉበትም ። ሀገርን ለመከፋፍልና ሕዝብንም ለማለያየት ግን ዕኩይ ምክንያት ይሆናል ።

የየካቲት ዐብዮት የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ዐብዮት ነው። ያልተከፋፈለ ያልተሸራረፈ፤ ያልተመሰቃቀለና ያልተዳቀለ ምልዑ ኢትዮጵያዊ ዐብዮት ሆኖ ይኖራል ። ወርዱ- ቁመቱ፤ ስፋቱና ርዝማኔው፤ በዘርና በቋንቋ ክልል የሚወሰን አይደለም። የየካቲት ዐብዮት በኢትዮጵያ ማዕቀፍ እየተሽከረከረ የሚኖር እንጅ ዘርና ጎሳ ፍለጋ በየክልሉ የሚንከራተት አይደለም። የክልል ጥብቆ ሊያጠልቁበት ቢሞክሩም፤ ስለሚጥበው ይተረትረዋል ። አሽቀንጥሮ ይጥለዋል !

የ1966ቱ የካቲት ዐብዮት ፤ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ላይ አስተባብሮ እንዲቆም ያደረገ በመሆኑ፤ ዘለዓለማዊ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ተቋም ሆኖ ይኖራል። ይህንን ብኩርና ( የበኩር ልጅነቱን ) ለምንም ሆነ፤ ለማንም አሳልፎ አይሰጥም ። እኛ፤ ዛሬ የወረሃ የካቲትን ታሪካዊነት የምናከብረው ከዚህ መሠረታዊ ዕምነት ቢሆንም፤ የሀገራችንን መፃዒ ብሩኅ ተስፋ በኢትዮጵያ አድማስ እያንዣበበ መምጣቱን በመገንዘብም ነው። ከፍተኛ መሥዋዕት የተከፈለበትም ትግል ውጤት እንደሚያስመዘግብ ብዥታ አይኖርም። ይህም ሲባል አለምክንያት አይደለም።

1ኛ. የዘር ፖለቲካ ሥርዓት፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እያተናቀና እየተጠላ መምጣቱ። የዚህ ሥርዓት አራማጆች ፤ በስሙ የነገዱበት የትግራይ ሕዝብ እንኳን ሳይቀር ፤ ከዕለት ወደ ዕለት እየተቃወመው መሄዱ ።

2ኛ. ወጣቱ ትውልድ በዘርና በቋንቋ መደራጀት የቱን ያህል አሳፋሪና ኋላ ቀር መሆኑን መረዳቱ ። ሀገር በታኝና ሕዝብ ከፋፋይ ሥርዓት አድሃሪና ለዕድገትም ጠር መሆኑን ተገንዝቦ፤ እየነቃ መምጣቱ። በዚህ ዕምነት ላይ በመመስረት ብዙ ወጣት ደራሲያን፤ የኪነትና የሥነ ጽሁፍ ሰዎች እየበረከቱ መምጣታቸው። በርካታዎቹም፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ለዴሞክራሲ አስተዳደር እያታገሉ መሆናቸው ።

3ኛ. ወያኔ ፤ ብል እንደበላው ፈትል፤ ውስጡ እየተብሰከሰከ መሆኑ ። በሙስና የተበከለ፤ በወሲብና በስካር የላሸቀ፤ እርስ በእርስ እየተነካከስና እየተጠባባቀ፤ አንዱ ሌላውን እያሰረና እያሳደደ መምጣቱን ከግምት በማስገባትና በማጤንም ጭምር ነው። ታዲያ ይህ ወዴት ያመራል? ማለት ብቻ ሳይሆን፤ በተቃዋሚው በኩል፤ ምን እየተደረገ ነው ? የሚለው ጥያቄ ወሳኝ መልስ የሚያስፈልገው መሆኑም በገሃድ የሚታይ ነው ።

4ኛ. በዘማዊነቱ የሚታወቀው የዓለም ፖለቲካ ተለዋዋጭነት፤ የወያኔን ደጋፊዎችና የበላይ ጠባቂዎችንም ስለሚመለከት፤ በቁርጥ ቀን ኢጋፈጠውት እንደሚሄዱ መገንዘብም አስፈላጊ ነው። ዘላቂ ጥቅም እንጅ፤ ቋሚ ወዳጅም ሆነ ቋሚ ጥላት የሚባል ነገር የለም፤ የተባለውን የዲፕሎማቲክ የትብሃል ያጤኗል !

ለዚህም ነው እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት መሰረታዊ አስተያየቶች የተግባር ድምር ውጤት የሀገራችንን ሁኔታ በወሳኝ መልኩ እንደሚለውጠው ምንም አይነት ጥርጣሬ እንደሌለን አፅንዖት በመስጠት የምንገልፀው።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !